**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**
**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**
Efdpu@aol.com www.Finote.org
*ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ*
*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band*

ነሐሴ 22 ቀን 2005 ዓ.ም.
August 27, 2013 ዓ.ም.

## *እርዳታ ለለጋሳችሁን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ታላቅ ምስጋና*

ከሁሉ አስቀድመን የአክብሮት ሰላምታ እናቀርባለን።

ሁላችሁም እንደምትገነዘቡትና እንደምታውቁት ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ከተቋቋመ ጀምሮ ላለፉት 18 አመታት ሕዝባችን የሀገሩንም ሆነ የራሱን የወደፊት እጣ ለመወሰን የሚያስችለው ማናቸውንም ሀገር ነክ የሆኑና አለም አቀፍ ዜናዎች እንዲያገኝ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ሕዝባችን በሚያደርጋቸው ፀረ ኢሕአደግ ትግሎቹ ኢትዮጵያዊ አንድነቱንና ሀገራዊ ላኡአላዊነቱን ጠብቆ እንዲጓዝ በተከታታይ የሚያስተላልፋቸው አቅጣጫ ሰጪና ጠቋሚ ትችቶች የሚያቀርባቸው ዜናዎች፤ ትምህርት ሰጪ የሆኑ ቃለ መጠይቆች ከአዳማጩ ሁሌም ምስጋና እየተቸረው ይገኛል። በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ስለሚደረጉት እንቅስቃሴዎችም የጋራ አስተያየት እንዲይዝ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ እየተከታተለ የሚያቀርባቸው ዜናዎች ተወዳጅነታቸው ይበልጥ እየጨመረ ለመሆኑ የሚደርሱን ዜናዎች ይጠቁማሉ። በዚህም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ትብብራቸው እየጨመረ መሆኑ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። ከዘወትር አዳማጮቹ ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ ከሚያዳምጡን ዜጎቻችን በሚቀርብለት ቀና ትችትም በተሳሳተበት እያረመ ስርጭቱንና በአዘጋጆቹ ላይ በጥላቻ የተሞላ ትችቶች እንዳመጣጣቸው እያስተናገደ ይኸው እስከዛሬ ድረስ ተግባሩን በፅናት እየቀጠለ ይገኛል።

ፍኖተ ዴሞክራሲ ይህንን ሲያደርግ ከማንም ሳይሆን ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚደረግለት እርዳታ እንጂ ከጎረቤት ሀገርም ሆነ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ሕዝቧንም በቀና ከማይመለከቱ ባዕድኖች አንዲት ቤዛ አላገኘም። ለመለመንም አልቃጣም። በዚህም የማይናወጥ ተግባሩና አስተሳሰቡ ተጠሪነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በማድረጉ፣ የሕሊና ነፃነቱንም በማስጠበቁና የማንም ጥገኛ ባለመሆኑ ይኮራል። በዚህም የናንተ ድጋፍና ትብብር እሳከለ ድረስ ይቀጥልበታል።

ይህንን የፀና አላማውን ለማስቀጠል ይቻለው ዘንድ ከጥቂት ወራት በፊት በኢ.ኤፍ.ዲ.ኤን፤ ከአሲምባና ከአለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት የውይይት መድረኮች በመተባበር ለፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ በራሳችሁ አነሳሽነት የገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅት ባደረጋችሁበት ወቅት በተለያዩ ቀናቶች ጠርቀም ያለ ገንዘብ በድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ መሆኑን ስናረጋግጥ ከአክብሮት ሰላምታና አድናቆት ጋር ነው።
ወደፊትም ተመሳሳይ እርዳታ እንደምታደርጉልን ተስፋችን የጎላ ነው።

የሬዲዮ ስርጭትን አመስልክቶ ለምታቀርቡልን ማናቸውም ጥያቄዎች ካሁን እንዳደረግነው ሁሉ ወደፊትም በምታዘጋጁልንና በምንጋብዝበት መድረክ ተገኝተን ለመወያይት ምንጊዜም ዝግጁ መሆናችንንም ስንገልፅ ትብብራችሁም ምንጊዜም እንደማይለየን ሙሉ እምነታችን ነው።

በጋራ ትብብራችን የሕዝባችንን ብሩህ ተስፋና ራዕዩን ተግባራዊ የምናደርግበት ወቅት ሩቅ አይሆንም።

ከታላቅ ምስጋና ጋር

የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ
አዘጋጆች